# አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ!

***የወያኔ ብቸኛ ገዥነት ብሔራዊ ስሜት የሌለው፥ ለኢትዮጵያ አንድነት፥ ደህንነትና ብልጽግናን የማያስብ፥ የራስን ጐሳ ጥቅምና ሥልጣን አስከባሪና በብዝበዛ ላይ የተመሰረተ ክልሉን እያጠናከረ፤ ጐሳን ከጐሳ፥ ሐይማኖትን ከሐይማኖት እያጋጨ የራሱን ዕድሜ የሚያራዝም ቡድን ነው።***

*በጐሳ ተከፋፍለን ኢትዮጵያዊነት በጠፋበት፥ በጐጥ እየተያየን ወገን በኤድስ፥ በረሐብና በጐርፍ፥ በእስራትና በግድያ የተረፍንም በስደት እያለቅን፤ ለሕዝብ ነፃነት ሲታገሉ የተሰውትን መስዋዕታት መርሳት፥ እንደማናችንም ተሰደው ሆነ ሠርተው መኖር ሲችሉ በወያኔ እስር ቤት ለሚማቅቁት ወገኖቻችን ያለመታገልና በተቃዋሚ ኃይሎች ውህደት የተጀመረውን የቅንጅት መንፈስን መበረዝ የወያኔን እድሜ ማራዘም ነው።*

*እንደ 66ቱ የአብዮት ዘመን "ከቆራጥ መሪያችን ጋር ወደፊት!" የሚል ዓይነት የድጋፍ መግለጫዎች በቅንጅት ስም ከጥቂት ግለሰቦች ከሳንዲያጐ፥ ከሲያትል፥ ከካናዳ ወዘተ. በቅንጅት ድኅረ-ገጽ ላይ መታየታቸው የአፍራሽ ኃይሎችን ማንነት ግልጽ አድርጐታል። ይህ ደግሞ ከመሠረቱ ቅንጅት በሰሜን አሜሪካ ሲዋቀር ሳይፈታ የታለፈ ስህተት ስለሆነ ከአሁኑ ችግር ላይ ወድቀናል። ችግሮቻችን በግልጽነት ማቅረቡ ግለሰቦቹ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ እንዲሸሹ ወይም ሌላ ስም በመስጠት ድርጅቱን ለመከፋፈልና የቅንጅትን መንፈስ ለመበረዝ፣ የዲያስፖራን ፖለቲካ ለማዳከምና የታሰሩ ወገኖቻችን እንዳይፈቱ ድምጽ ለማሳጣት አይደለም።*

*በሰሜን አሜሪካን የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ አካል ሲፈጠር በወቅቱ የመላው አማራ አንድነት ድርጅት የድርጅት መዋቅሩን ሳይቀይርና የቅንጅቱን ደንብንና ሥነ ሥርዓን ሳይከተል የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የበላይነቱን ስለተረከበ ይህ መሠረታዊው ስህተት በውጭ ያለንን ኢትዮጵያውን በቅንጅት መንፈስ ተሰባስበን አገር ቤት ለሚካሄደው ትግል አጋርነትና ተሳትፎን ከሚያዳክሙ ምክንያቶችም ዋነኛው ሆኖ ተገንቷል። ለምሳሌም፣*

1. *ኢትዮጵያውያን በወሳኝ ትግል ላይ ባሉበት ወቅት ቅንጅት ከሚከተለው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውጭ በአምባገነንነት ስሜት በመነሳሳት ዓለም አቀፍ ቅንጅትን በማገድና የአመራር አባላትን ያለአግባብ ከሥራቸው ማባረር፥*
2. *የቅንጅትን አርማ ከላይ አድርጐ አንድነት የሚል የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ድኅረ ገጽና ቅንጅት ዓለም አቀፍ ድኅረ ገጽን በቁጥጥር ሥር ማደርግና እነሱ የፈለጉትን ብቻ በማውጣት ብዙሃኑን በማገልገል ፈንታ ለግል ጥቅማቸው ብቻ በማዋል ትግሉ ወደፊት እንዳይንቀሳቀስ ማገድ፥*
3. *በመቶዎች የሚቆጠሩ የነፃነት ታጋዮችና ሰላማዊ ሕዝቦች በወያኔ በግፍ የተጨፈጨፉበትንና በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖች ታፍነው ወደ ወህኒ የተጋዙበትና የሰማዕታትን ዓመት ሕዝቡ በአንድነት እንዳያከብርና ድምፁን ለዓለም ሕዝብ እንዳያሰማ ወቅትን ጠብቆ ሕዝቡን መበታተንና የቅንጅት የነፃነት መንፈስነትን ማፈን፣*
4. *በአጠቃላይ ትግሉን ከዲሞክራሲያዊ መሪነት ወደ ቡድናዊ አምባገነንት አመራር ማዛወር፤*

ይህንን ድክመቶቻችንን ስጠቅም እንደ ሠለጠነ ዜጋ ከስህተታችን ተማምረንና ተራርመን ይቅር ለእግዚአብሔር በመባባል የተቃዋሚ ኃይሎችን አንድነትን ለማጠናከርና ከጠላት ውርደት እንድንድን በማሰብ ነው። ወገኖቼ! በራሱ ላይ ሂስና ግለ ሂስ የማይቀበል ፓርቲ ሆነ ግለሰብ ለሕዝቡ ዲሞክራሲያዊ አመራርን ያመጣል ተብሎ አይታሰብም።

በውጭ ያለን ኢትዮጵያውያን ምንም እንኳን የመናገር ሆነ የመሰለፍ ሐሳብንም በነፃ የመግለጽ ዲሞክራሲያዊ መብት እያለን፤ የሚገጥሙንን ችግሮችንና ቅራኔዎችን በውይይት መፍታት፥ ፖለቲካዊ ግትርነት፥ እርስ በርስ መማማርና ከሌላው አገር የፖለቲካ ሂደቶች ሃሳብን አንሸራሽሮ በኋላም ተወቃቅሶ፣ ተመልሶም ተሳስቆ፥ ተጨባብጦ መለያዬት አለመደብንም። ከጠባብ አመለካከት አጣብቅኝ ተላቀን፣ለሀገር የሚበጀውን መተግበር ተገቢ ሆኖ ሳለ፥ በአብሮ አደግነትና ትውውቅ፥ በግላዊ ጥቅሞች ግኑኙነት፥ በፖለቲካ ጠባብነትና በኋላ ቀር አይዶሎጂ ላይ የተመሰረተ ቡድናዊ ሴራ ትስስር አገርን ለመምራት የማይቻል ለመሆኑ ለማስገንዘብ እወዳለሁ። ይህ ጽሑፍ እነ ሻለቃን ለመቃወም ወይም ሌሎችን ለመደገፍ የወጣ ሳይሆን ምን ጊዜም ቢሆን አገርን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ከመለያዬት ተሰባስቦ በመወያዬት ችግሮችን የመፍታት ባህርይ እንዲኖረን ለመጠቆም ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ ነፃነትዋን ጠብቃ የኖረችና እስከ ዛሬም በሰው አገር ጣልቃ ገብታ የማንንም አገር ያልወረረች፥ ወታደሯም የአገሯን ድንበር አስከባሪ እንጂ እንደ ዛሬው ባንዳ ሆነው የሰውን አገር ወረው አያውቁም። ለችግሯም ደራሽ ከልጆችዋ በቀር ማንም ሰው የላትም። እስካሁን ድረስ በምዕራባውያን መንግሥታት ብድርና ዕርዳታ የበለጸገ አገር የለም። ኃያላን መንሥታት በሦስተኛው ዓለም ገንዘባቸውን የሚያጠፉት ከራሳቸው ብሔራዊ ጥቅም አንጻር ነው። ስለዚህ ነው እስካሁንም የምዕራባውያን መንግሥታት በኢትዮጵያ ላይ ያለውን ፖሊሲ ለማስቀየር ያልተቻለው። አቶ መለስም በአፍሪቃ ቀንድ ባለው ቀውስ በኢትዮጵያ ልጆች ደም እየነገደ የጦር መሣሪያና ጥሬ ገንዘብ ይጐርፍለታል። “ጌታዋን የተማመነች በግ ላትዋን እደጅ ታሳድራለች” እንዳሉት ዛሬ በሶማሌ ላይ በመዝመቱ የዓለም የእስልምና ተከታይ አገሮች በጠላትነት እንደ አሸን እየፈሉብን ነው። የጅማውም የክርስቲያኖች እልቂት እንደ ምሳሌነት ከዚህ ጋር ይያያዛል። አሜሪካን እንኳን ልትወጣው ያልቻለችውን ጦርነት ውስጥ ኢትዮጵያ እየገባች ነው። ስለዚህ አሜሪካን በቅርቡ Africa Center for Strategic Studies (ACSS) በማለት ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ማዕከሉን በእምባሲው ሥር በማስፋት አዲስ የአፍሪቃ ማዕከላዊ ቢሮ አዲስ አበባ ከፍቷል። ይህንኑም (US Strategic Studies Center in Ethiopia, በሚል ርዕስ Middle East Times, የሚባል ጋዜጣ Nov. 1, 2006) ግልጽ አድርጐታል። ይህም ድርጊት ለመለስ ዜናዊ የአገዛዝ ዘመን እድሜን የሚያራዝም ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብን ከወያኔ ጋር ብቻ ሳይሆን ከአሜሪካም መንግሥት ጭምር ከፍተኛ ቅራኔ ውስጥ ጥሎታል።

የጋራ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት መደራደሩ ዘመናዊና ሥልጡነ ሕዝባዊነት ነው። ዜጋዊ ሕልውናችንም የሚከበረው ሁሉም እኩልነት ላይ በተመሰረተ ፍትሐዊ ሥርዓት ሆኖ ሳለ የኢትዮጵያውነትን ሥነ ልቦና ማኮላሸት፥ በሕዝቦች መሐል ልዩነትን መፍጠር፥ የአንድነታችንን የጋራ ታሪክን መካድ የወያኔ መርህ ተግባሩ ስለሆነ ይህንን መከተሉ የዛሬው ወያኔ ደግም መሆን ነው። እውነተኛ ኢትዮጵያን ወዳድ የሆነ ዜጋ

ሁሉ ከግሉ፣ ከፓርቲው፥ ከድርጅቱ፥ ከጐሳው ጥቅም በላይ አድርጐ ማስቀመጥ ያለበት የኢትዮጵያን ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም ነው ብዬ አምናለሁ። አመሰግናለሁ

ደመላሽ ካሳ

ኢትዮጵያዊ አሜሪካውያን ድኅረ - ገጽ